# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

## ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ሲገባቸው ያልተመዘገቡ ግብር ከፋዮች በታክስ ሥርአቱ እንዲታቀፉ የተዘጋጀ የማትጊያ ስትራቴጂ ትግበራ መመሪያ

(የ2003 የተጨማሪ እሴት ታክስ ማበረታቻ ስትራቴጂ)

ጥቅምት 2003 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

## ክፍል ሶስት

## በማበረታቻ ጊዜ ውስጥ ስለሚፈፀሙ ተጓዳኝ ተግባራት

### 7. ስትራቴጂውን/መመሪያውን ለማስፈፀም ስለሚደረግ ቅስቀሳ

ለተ.እ.ታ ያልተመዘገቡ ግብር ከፋዮች በስትራቴጂው የተሰጠውን ማበረታቻ በመጠቀም በተሰጠው የጊዜ ገደብ እንዲመዘገቡ፣ እድሉን አለመጠቀምና አለመመዝገብ ያልተከፈለውን ገንዘብ መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ጭምር እንደሚያስጠይቅ በጋዜጦች፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ተከታታይ ቅስቀሳ ይደረጋል።

### 8. የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ ስለመጠቀም

በስትራቴጂው/በመመሪያው የተሰጠውን ማበረታቻ በመጠቀም በራሱ ጊዜ የሚቀርብ ተመዝጋቢ ወዲያውኑ የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ ማሽን መጠቀም የሚጀምርበት ሁኔታ ይመቻቻል፡

### 9. መረጃ ማሰባሰብና ማደራጀት

1) ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ግብር ከፋዮችን ለመለየት እንዲቻል እንደ መነሻ የሚያግዝ መረጃ የማሰባሰብና የማጥራት ሥራ ይከናወናል። መረጃ የማሰባሰቡ ሥራ በማበረታቻው ጊዜ ውስጥ በዘርፍ ደረጃ ዓመታዊ ሽያጫቸው ከብር 500 ሺ.ህ በላይ የሚሆኑትን የንግድ ዘርፎች ቁጥር እስከአሁን ካሉት 9 ዘርፎች በላይ እንዲሆኑ የማድረግ የጥናት ሥራን ያጠቃልላል፤ ውጤቱም ተግባራዊ ይደረጋል።
2) መረጃውን የማሰባሰብና የማጥራት ሥራ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ፣ የአዲስ አበባ ገቢዎች ባለሥልጣን በተወከሉበትና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር በተሰየመ ሰብሳቢ በሚመራ ግብረ ኃይል ይከናወናል።

## ክፍል አራት
## የተሰጠው የማበረታች የምዝገባ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ስለሚከናወኑ ተግባራት

### 10. የግዴታ ምዝገባ ማካሄድ

1) ለማበረታቻ የተሰጠው የ3 ወር ጊዜ እንደተጠናቀቀ በ91ኛው ቀን በሕጉ መሠረት የግዴታ የምዝገባ ሥራ የሚከናወን ሲሆን በተለይ በማበረታቻ ጊዜ ውስጥ በዘርፍ ደረጃ ዓመታዊ ሽያጫቸው ከብር 500 ሺህ በላይ የሚሆኑ የንግድ ዘርፎች የመለየት ሥራን ይጠቀልላል፡፡
2) የግዴታ ምዝገባ የማካሄድ ሥራ በዚህ ስትራቴጂ የተደራጀውን መረጃ መሠረት በማድረግ በመዝጋቢ ግብረ ኃይል ቡድን ይከናወናል፡፡ የመዝጋቢ ቡድን በአዲስ አበባ በሁሉም ወረዳዎች ይደራጃል፡፡

### 11. ሕጋዊ እርምጃ ስለመውሰድ

በዚህ ስትራቴጂ/መመሪያ መሠረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይመዘገቡ የቀሩ ግብር ከፋዮች በግዴታ እንዲመዘገቡ ከማድረግ በተጨማሪ እንደፈፀሙት ጥፋት ክብደት በሕግ መሠረት በወንጀል፣ በፍትሐብሔርና በአስተዳደር እንዲቀጡ አስፈላጊው ይከናወናል፡፡ ፡፡

### 12. የክትትልና ግምገማ ሥራ

የስትራቴጂው/የመመሪያው አፈፃፀም በየአስራ አምስቱ ቀን ዋና ዳይሬክተር በተገኙበት ይገመገማል፡፡

## ክፍል አምስት
## የባለድርሻ አካላት ሚና

### 13. ለስትራቴጂው/ለመመሪያው አፈፃፀም የባለድርሻ አካላት ተሣትፎ

በታክስ አስተዳደሩ ጉዳይ ላይ ከግብር አስገቢው ባለሥልጣን መ/ቤት ጋር እኩል ባለድርሻ የሆኑት የንግዱ ማኅበረሰብ ተወካዮች ማህበራት እንዲሁም ሌላው የኅብረተሰብ

